*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

## የጋራ ግንዛቤ በጋራ ውይይት ለማግኘት የተዘጋጀ ሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ በፍራንክፈርት ከተማ-ጀርመን

ከተመሰረተ 42 አመቱን በማስቆጠር ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን ለመጎናፀፍ፡ መሰረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹንና የሀገሩን ሉአላዊነት ለማስከበር በሚያደርገው የትግል እንቅስቃሴ በግንባር ቀደምትነት የበኩሉን አስተዋፅዖ በፅናት እያበረከተ ይገኛል። ላለፉት 23 አመታት በወያኔ ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝ የተነሳ ሕዝባችን በአሁኑ ወቅት ከሚገኝበት እጅግ አሳሳቢና አሳዛኝ ሁኔታ በኢትዮጵያዊነታቸው በእጅጉ የፀኑና ለሕዝባቸው ቀናኢ የሆኑ እንደ ኢሕአፓ የመሰሉ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ከምንጊዜውም በበለጠ ትግሉን የመምራት ኃላፊነት የሚጠበቅባቸው ለመሆኑ በወቅቱ ከምንገኝበት ሁኔታ የበለጠ ማስረጃ ሊኖር አይችልም። ይህ ሕዝባችንንና ሀገር ወዳዱን ከፍተኛ መስዋዕትነትን እያስከፈለ ያለ እልህ አስጨራሽ ትግል በተለያየና ሁለገብ በሆነ መልክ ስኬታማ ይሆን ዘንድ በይበልጥ መጠናከርና በጠቅላላ ሀገሪቱ መስፋፍት እንደሚኖርበት የኢሕአፓ ጽኑ እምነት ነው። በመሆኑም የሕብረት ትግል እንዲደረግ በተደጋጋሚ ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው። ይህንን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ደግሞ እነዚህ ድርጅቶች ከሕዝብ ጋር በተለይም የወደፊት ሀገር ተረካቢ ከሆነው ወጣት ትውልድ ጋር መወያየትና የጋራ ግንዛቤ ለማግኘት በመጣር ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት መግፋት የግዴታ እንደሚል ግልፅ ነው።

በመሆኑም ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 42ኛ አመት ምክንያት በማድረግ ፡

ሀ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ አቢይ ሳህሉ
ለ. የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ፕሬዘዳንት የሆኑት የተከበሩ
   አቶ አሊ ሁሴን፡ በዘመኑ የመገናኛ ዘዴ
ሐ. የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ አባል አቶ ይርጋለም ታደሰ

የሚገኙበት በወቅቱ የሀገራችን ፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ ላይ በጀርመን ሀገር ከሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ጋር ሰፊና ጥልቅ ውይይት በማካሄድ የጋራ ግንዛቤ ለማግኘት ያስችለን ዘንድ አንድ ሕዝባዊ ስብሰባ እኛ በጀርመን ሀገር የምንገኘው የኢሕአፓ ፓርቲ ኮሚቴ አባላትና ደጋፊዎች፡ በፍራንክፈርት ከተማ ያዘጋጀን በመሆናችን በዚህ ዝግጅታችን በመገኘትና ንቁ ተሳታፊ በመሆን የበኩላችሁን አስተዋፅዖ ታበረክቱ ዘንድ በትህትና እንጋብዛለን።

# ቅዳሜ ኦገስት 23 2014 ዓ.ም.
# 13፡00-19፡30
## Haus der Jugend Frankfurt
## Deutschherrenufer 12
## 60594 Frankfurt / M.

ስለ ዝግጅቱ የበለጠ ለማወቅ፣ 015213865107; 015219281406